Hamlin Fistula Ethiopia

# ሐምሊን ዜና መጽሔት

ቁጥር 3 ፤ ጥቅምት 2010 ዓ.ም.

በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለሠራተኞች የሚሰራጭ




## በውስጥ ገፆች


- የ2009 ዓ.ም በጎ ሰው 2
- ደማቅ አቀባበል ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች 3
- የደመወዝ ማሻሻያ ተግባራዊ ተደረገ 4
- ቀጣይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ 5
- የአዲስ ዓመት አቀባበል 6
- ተማሪዎቹን 100% በማሳለፍ ብቸኛው የአገሪቱ ኮሌጅ 7
- በዋናው ግቢ ህንፃ ሊገነባ ነው 8
- በወንዝ ዳር ያለ ሆስፒታል 9

# ዶ/ር ካትሪን የ2009 ዓ.ም በጎ ሰው ተባሉ



በግለሰቦች የራስ ተነሳሽነት ተቋቁሞ ላለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት ለሀገራቸው የተለየ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ግለሰቦችን አወዳድሮ የዓመቱ በጎ ሰው በሚል ማዕረግ ዕውቅናን የሚሰጠው የበጎ ሰው ሽልማት ድርጅት ዘንድሮም ለአምስተኛ ጊዜ በአስራ ሁለት ዘርፎች ተወዳድረው ያሸነፉ ግለሰቦችን ነሐሴ 28፣ 2009 ዓ.ም በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል የዓመቱ በጎ ሰው በሚል ይፋዊ እውቅናና ሽልማት ሰጥቷል፡፡

የዘንድሮው የበጎ ሰው ሽልማት ካለፉት ዓመታት በተለየ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የውጭ ሀገር ዜጋ ሆነው ለኢትዮጵያ በጎ የሰሩ የሚል አዲስ የሽልማት ዘርፍ አካቶ የውጭ ዜጎችንም ሸልሟል፡፡ በዚህ ዘርፍ የመጨረሻ እጩ ከነበሩት ሶስት የውጭ ዜጎች መካከል የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ መስራችና ከአምስት አስርተ አመታት በላይ በወሊድ ሳቢያ በሚከሰት ፊስቱላ መዘዝ ከባድ አካላዊና ስነልቡናዊ ጎዳት ለደረሰባቸው የሀገራችን ሴቶች ሁሉን አቀፍ ነፃ ህክምና እንዲያገኙ ያስቻሉት የ93 ዓመት እድሜ ባለፀጋ ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን አሸንፈው የዓመቱ በጎ ሰው ተብለዋል፡፡ የዕድሜ ጫና ሳይገድባቸው ዝግጅቱ ከተጀመረ በኋላም ቢሆን ሽልማቱን በአካል ተገኝተው የተቀበሉት ዶ/ር ካትሪን በቦታው መገኘታቸው እንደታወቀ መደበኛው ፕሮግራሙ ተቋርጦ አዳራሹን የሞላው ታዳሚ በሙሉ ተነስቶ እያጨበጨበ አክብሮቱን በመግለፅ ሽልማቱ እንደሚገባቸው አረጋግጧል፡፡

ካባ ደርበው ሽልማቱን ከተቀበሉ በኋላ ዶ/ር ካትሪን ባደረጉት ንግግር በሽልማቱ በጣም እንደተደሰቱ ገልፀው አሁን ለተገኘው ስኬት ገና ከጅምሩ አብረዋቸው ያለመሰልቸት ሲሰሩ የኖሩና እየሰሩም ያሉ ኢትዮጵያውያን ሚና የማይተካ እንደሆነና ሽልማቱ የእነርሱም ጭምር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ስለሽልማቱ ተጠይቀው አስተያየት የሰጡን የድርጅታችን ሠራተኞች እንደሚሉት ዶ/ር ካትሪን ከዚህም በላይ እውቅና ሊሰጣቸው የሚገባ ደግ ሰው ናቸው፡፡ የሀገራችንን ችግር ለመቅረፍ እድሜ ዘመናቸውን የለፉ አቻየለሽ ቸር እንደመሆናቸው እኛ ሠራተኞቻቸው ደግሞ ከአርአያነታቸው ተምረን አደራቸውን ተረክበን የጀመሩት ዳር እንዲደርስ ከልብ በጋራ በመስራት የወሊድ ፊስቱላ በአገራችን እንዳይኖር እናደርጋለን ብለዋል፡፡

# የ2010 አዲስ ተማሪዎች በደማቅ አቀባበል ሐምሊንን ተቀላቀሉ

የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ህጋዊ ፈቃድ ተሰጥቶት ስልጠና ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየዓመቱ ነባሮቹን ሲያስመርቅ አዲሶቹን ሲቀበል ቆይቷል፡፡ በ2010 የትምህርት ዘመንም ኮሌጁ ባለው ውስን የመቀበል አቅም እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ የራሱን መልማይ ቡድን በየክልሉ በመላክ በ2ተኛ ደረጃ ት/ት ማጠናቀቂያ ፈተና ውጤታቸው ከፍ ያለ ነጥብ ያመጡና ሚድዋይፍ የመሆን ፍላጎት ያላቸው 24 የክፍለሃገር ሴት ተማሪዎችን ለይቶ በመስከረም ወር አጋማሽ ተቀብሎ የቅድመ-ትምህርት ዝግጅት አድርጓል፡፡



በተቋሙ ተገኝተው የእንኳን ደህና መጣችሁ ያሉት የድርጅታችን ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ እንደተናገሩት እናንተ የሐምሊን ሚድዋይፎች ከተቋሙ በምታገኙት ደረጃውን የጠበቀ ስልጠና ተጠቅማችሁ ትልቁን የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያን ግብ በዋናነት የምታሳኩ እንደመሆናችሁ ሁልጊዜም ትኩረታችን አይለያችሁም፤ ከእናንተ የሚጠበቀው ትምህርታችሁ ላይ ማተኮርና በብቃት ማጠናቀቅ ብቻ ይሆናል ብለዋል፡፡ የኮሌጁ ምክትል ተጠሪ ሲስተር ማሪት በበኩላቸው ተማሪዎቹን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ተቋሙ እናንተን በሙያው የላቀ ክህሎት ባለቤት እንድትሆኑ ለማስቻል የተለመደውን ሙሉ ዝግጅት በማድረጉ ከአራት ዓመት ስልጠና በኋላ በንድፈ-ሀሳብም ሆነ በተግባር የተሟላ ክህሎት ባለቤት ሚድዋይፎች ሆናችሁ እንደምትመረቁ እምነቴ ነው ብለዋል፡፡

በ2010 ዓ.ም የት/ት ዘመን ሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ የተቀላቀሉት 24ቱ አዲስ ተማሪዎች በየመጡበት አካባቢ ሲታይ 10 ከአማራ ብ.ክ.መ፣ 4 ከትግራይ፣ 7 ከደቡብ እና 3 ከኦሮሚያ እንደሆነ የተቋሙ መረጃ ያሳያል፡፡

በመጀመሪያው ሁለት ሳምንታት ቆይታቸው ተማሪዎቹ ከተቋሙ መርሆዎች ጋር እንዲተዋወቁ ከመደረጉ ባሻገር በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ዋና ዋና ታሪካዊና የገበያ ቦታዎችን በማየት ከተማውን እንዲለማመዱ ተደርጓል ፡፡


# አዲስ የስራ ደረጃና የደመወዝ ማሻሻያ ተግባራዊ ተደረገ

ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ አዲስ የስራ ደረጃና የደመወዝ ማሻሻያ ከሐምሌ 1፣ 2009 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ፡፡



ኖሎት በተባለ ድርጅት ተጠንቶ የቀረበው አዲስ የስራ ደረጃና የደመወዝ ማሻሻያ ጥናት የሠራተኞችን ጥያቄ በተወሰነ እንደመለሰ የተናገሩት የሐምሊን የሰው ሃይል አስተዳደር ኃላፊ አቶ ተስፋዬ አባይነህ ውጤቱ ሁሉንም ሠራተኞች እኩል አስደስቷል ባይባልም በገለልተኛ አካል መከናወኑ ሂደቱ ከተፅዕኖ የነፃና ፍትሃዊ እንዲሆን አድርጓል ብለዋል፡፡ ቅሬታ ያላቸው ሰራተኞች ማመልከቻ እንዲያስገቡ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ቅሬታቸው እየታየ መሆኑን አክለው ገልጸዋል፡፡

ኖሎት የተባለው ድርጅት በወጣው ግልጽ ጨረታ ተወዳድሮ በማሸነፍ ጥናቱን ላለፉት አምስት ወራት በዘርፉ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎቹ ሲያከናውን መቆየቱ ይታወሳል፡፡



# ቀጣይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በተግባር ላይ መዋል ጀመረ



ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት (ከ2010 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም) የሚተገብረውን ቀጣይ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አጠናቆ ተግባር ላይ ማዋል ጀመረ፡፡

ቀጣዩ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የድርጅቱን ራይዕና ተልዕኮ በማሳካት ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው የዕቅድና ፕሮግራም ክፍል ኃላፊ ዶ/ር ደምሰው በየነ ተናግረዋል፡፡ "ቀጣዩ ዕቅድ ከሦስቱ የድርጅቱ ዋና ዋና የፕሮግራም መስኮች ማለትም ህክምና፣ መከላከል እና ማገገሚያና መልሶ ማቋቋሚያ ባሻገር ጥናትንና ሀብት ማሰባሰብን አካቷል" ብለዋል፡፡

የዕቅዱን ይዘትና አፈጻጸም በተመለከተ ከሁሉም ሠራተኞች ጋር በየደረጃው ውይይት እንደሚደረግ የገለፁት የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ፣ ሠራተኞች ከመቼውም በበለጠ በትግበራው ሂደት ውስጥ ጉልህ ድርሻቸውን እንዲወጡ ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

የዕቅዱን ዝግጅት አዲስ ኮንቲኔንታል የጤና አጠባበቅ ኢንስቲትዩት (Addis Continental Institute of Public Health) በዋናነት ያማከረ ሲሆን በሂደቱም በተለያዩ ደረጃዎች ላይ የሚገኙ የድርጅቱ ሠራተኞች ተሳታፊ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ጥረት አድርጓል፡፡

# የ2010 አዲስ ዓመት አቀባበል በድምቀት በዋናው ግቢ ተከበረ



የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሚዩኒኬሽንስ ጉዳዮች ቢሮ ሠራተኞችና ኃላፊዎች አዲሱን 2010 ዓ.ም. ቅበላ ከፊስቱላ ታካሚዎች ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ፊስቱላ ሆስፒታል ግቢ ውስጥ በተለያዩ ፕሮግራሞች በድምቀት ነሐሴ 30፣ 2009 ዓ.ም. አከበሩ፡፡

እንኳን አደረሰን በማለት ክብረ-በዓሉን በንግግር የከፈቱት የሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሚዩኒኬሽንስ ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በዓሉን ከሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ሠራተኞችና ታካሚዎች ጋር ለማክበር ስለመጡ ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡ “አስታዋሽ አያሳጣችሁ፡፡ እኛን መርጣችሁ፤ እኛን ብላችሁ ይህን የመሰለ ፕሮግራም አዘጋጅታችሁ መጪውን አዲስ ዓመት ከእኛ ጋር ለመቀበል ስለመጣችሁ በራሴና በሐምሊን ፊስቱላ ሠራተኞችና ታካሚዎች ስም አመሰግናችኋለሁ” ብለዋል፡፡

በአከባበሩ ላይ ዶ/ር ካትሪን የተገኙ ሲሆን ለሁለቱም ድርጅት ሠራተኞችና ኃላፊዎች እንዲሁም ለፊስቱላ ታካሚዎች አዲሱ 2010 ዓ.ም. መልካም ዘመን እንዲሆን ተመኝተዋል፡፡




# የሐምሊን ሚድዋይፈሪ ኮሌጅ ተማሪዎቹን መቶ ፐርሰንት በማሳለፍ ብቸኛው የጤና ሳይንስ ማሰልጠኛ ተባለ



የሀገሪቱ ጤና ጥበቃ ሚንስቴር በጤናው ዘርፍ በየዓመቱ ከመንግስትና ከግል ተቋማት ተመርቀው የሚወጡ ባለሙያዎችን ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት የብቃት ማረጋገጫ ፈተና በመስጠት ተቋሙንም ተማሪዎቹንም ይመዝናል፡፡ በቅርቡ በ 2008 ዓ.ም ተማሪዎቻቸውን አስመርቀው ለፈተና ያቀረቡ የመንግስትና የግል ጤና ሳይንስ ተቋማት ውጤት ይፋ ሆኗል፡፡ በውጤቱም ሚድዋይፍ ተማሪዎቻቸውን ካስፈተኑ 29 የግል እና የመንግስት ጤና ሳይንስ ማሰልጠኛ ተቋማት ውስጥ ሐምሊን ያስፈተናቸውን ሁሉንም በማሳለፍ ብቸኛው በመሆን ጥራት ያለው ትምህርት የሚሰጥ ተቋም በሚል በመንግስት እውቅና ተሰጥቶታል፡፡

እንደ ጤና ጥበቃ ሚንስትር መረጃ በመላ ሀገሪቱ የጤና ሳይንስ ስልጠና ከሚሰጡ የግልና የመንግስት ተቋማት ተማሪዎቹን መቶ ፐርሰንት ያሳለፈው ሐምሊን ብቻ ነው፡፡ አቶ ዘላለም በለጠ የተቋሙ መሪ ስለጉዳዩ በሰጡት አስተያየት ለየተቋማቱ መሪዎች የጤና ጥበቃ ሚንስትር ከፍተኛ ባለስልጣን በተገኙበት ይፋ የሆነው ውጤት አሁንም እንደከዚህ ቀደሙ ሐምሊን የጥራት አምባሳደርነቱን አጠናክሮ እንደገፋበት ከማሳየቱም በላይ ከመንግስት አካላት ጋር ለሚኖር ቀጣይ የስራ ግንኙነት ምቹ መደላድልን ይፈጥራል ብለዋል፡፡ ለመላው የተቋሙ ሰራተኞች እንዲሁም ለሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ባጠቃላይ ውጤቱ የሚያኮራና ለበለጠ ስኬት የሚያተጋ እንደሆነም አቶ ዘላለም አክለዋል፡፡

# በዋናው ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ለቢሮዎች የሚሆን ህንፃ ሊገነባ ነው




ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ለቢሮዎች አገልግሎት የሚሆን ባለሁለት ፎቅ ዘመናዊ ህንፃ በዋናው ሆስፒታል ግቢ ውስጥ ለማስገንባት በዝግጅት ላይ ነው፡፡ አሸናፊውን ተቋራጭ የመምረጡ ሂደት እየተጠናቀቀ ነው ያሉት የግዥ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወሮ በለጥሻቸው ታደሰ በሚቀጥለው ወር ውስጥ ሂደቱ ተጠናቆ ከአሸናፊው የግንባታ ድርጅት ጋር የውል ስምምነት እንደሚፈረም ገለፀዋል፡፡


የሚገነባው ህንፃ የቢሮ ክፍሎች፣ የኮምፒውተር ክፍልና የሐምሊን ጋለሪ እንደሚያካትትና የሚያርፍበት ቦታም በሆስፒታሉ ዋና መግቢያ በኩል ሁኖ አሁን የፋይናስ ክፍል ያለበትን ቦታ ያካልላል፡፡

ህንፃው ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ሲውል አሁን የሚታየው የቢሮዎች እጥረት በከፊል እንደሚቀንስ የገለፁት የኦፕሬሽንስ ማናጀር አቶ ጥላሁን ሞላ የግንባታው ሂደት በስራና በእንቅስቃሴ ላይ የተወሰነ አለመመቸት ሊፈጥር ስለምችል ሠራተኞች ይህን ተገንዝበው አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ለህንፃው ግንባታ እስከ 20 ሚሊዮን ብር የሚያስፈልግ ሲሆን ግንባታውም በዚህ የበጀት ዓመት ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል ተብሎም ይጠበቃል፡፡



# "የተስፋ ታሪክ - በወንዝ ዳር ያለ ሆስፒታል"
# (A Story of Hope- The Hospital by the River)




"የሚያብረቀርቁ የቆርቆሮ ጣራዎችን ከበታቻችን ስንመለከት በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ እያንዣበብን መሆናችንን ተረዳን:: አውሮፕላኑ ማሽቆልቆል ጀመረ:: ያለ ምንም እንከንም ቆመ::... አቧራና ባህር ዛፍ የተቀላቀለበት የለመድነውን የአውስትራሊያ ምድር አየር ተነፈስን:: እንደ አብዛኞቹ የአፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ ሃገሮች ሁሉ ኢትዮጵያም ከአውስትራሊያ በመጡ የባሕር ዛፍ ፍሬዎች የተሞላች ነች:: ዛሬ ላይ ሆኜ ሳስበው፡- ይህ የመጀመሪያው ስሜቴ ይሆን አዲስ አበባን ቤቴ እንድላት ያደረገኝ? እላለሁ... ”

ይላሉ ዶ/ር ካትሪን ሐምሊን፡ “የተስፋ ታሪክ- በወንዝ ዳር ያለ ሆስፒታል” (A Story of Hope- The Hospital by the River) በሚለው መጽሃፋቸው::

ዶ/ር ካትሪንና ዶ/ር ሬጅ ሐምሊን በአውስትራሊያ ሲድኒ ውስጥ ከሚገኙ ስመ ጥር ሆስፒታሎች በአንዱ ውስጥ በአዋላጅነትና በማሕጸን ስፔሻሊስትነት የሚያገለግሉ ሃኪሞች ነበሩ::

እ.አ.አ በ1957 “ዘ ላንሰት” በተባለው የእንግሊዝ የጤና መጽሔት ላይ የወጣው ማስታወቂያ፡- “አዲስ አበባ የሚገኘው የልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ነርሶችን በአዋላጅነት የሚያሰለጥን ት/ቤት ለማቋቋም የማሕጸን ዶክተሮችን ለመቅጠር ይፈልጋል” ይላል::

የሃኪሞች እጥረት ባለባቸው ሃገሮች ውስጥ የመስራት ፍላጎት የነበራቸው ሐምሊኖች ማስታወቂያውን እንዳነበቡ ለቦታው አመለከቱ:: በወቅቱ የነበረው የቀ.ኃ.ሥ መንግስትም ማመልከቻቸውን ተቀበለ::

ዶ/ር ሬጅ ባለቤታቸውንና ሕጻኑን ልጃቸውን ይዘው ወደ አዲስ አበባ ከማቅናታቸው ቀደም ብሎ የ6 ዓመቱን ሪቻርድን መጭ ህይወት አስመልክቶ ውሳኔ መስጠት ተቸግረው ነበር:: እናም

ጉዞው እየተቃረበ በነበረበት ሰሞን ታዳጊ ሕጻን ሪቻርድን ት/ቤት ካደረሱት በኋላ ረጅም መንገድ በመንዳት ጉዳዩን እያውጠነጠኑ ከአንድ ማረፊያ ሥፍራ ጎራ ይላሉ።

በአቅራቢያቸው ተቀምጦ ቢራ ይጠጣ የነበረ አውስትራሊያዊ "ምነው ጃል? በጣም ሃሳብ የገባህ ትመስላለህ" ይላቸዋል። ዶ/ር ሬጅም በቅርቡ ከባለቤታቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ ሊሄዱ እንደሆነና የ6 ዓመት ልጃቸውን በተመለከተ ግን አብሯቸው ይሂድ ይቅር የሚለውን ለመወሰን እንዳልቻሉ ይነግሩታል።

ሰውየውም "ከኢትዮጵያ የተመለስኩት በቅርቡ ነው። ውብ የሆነች አገር ነች። ኢትዮጵያ ውስጥ ለካርታ ሥራ ተልዕኮ 3 ዓመት ቆይቻለሁ። አገሪቷን ወድጃታለሁ። ማለፊያ የእንግሊዘኛ ት/ቤት አለ። ልጄ የተማረው እዛ ነው። እዚህ ከመጣ በኋላም ጥሩ ት/ቤት ለማግኘት ምንም ችግር አላጋጠመውም። ልጅህም በጣም ይወደዋልና ይዘኸው ሂድ" ብሎ ይመክራቸዋል።

ዶ/ር ሬጅም እጅግ ደስተኛ ሆነው ህሊናቸውን ካስጨነቀው ሃሳብ ተገላግለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

ዘመኑ እ.አ.አ 1957 ግንቦት ወር ነበር። ዶ/ር ካትሪንና ባለቤታቸው ዶ/ር ሬጅ ሐምሊን የስድስት ዓመት ሕጻን ልጃቸውን ሪቻርድ ሐምሊንን ይዘው አዲስ አበባ ገቡ።በርግጥም ወጣቱ ሪቻርድ እንደወላጆቹ ሁሉ ኢትዮጵያን ወደደ። ኢትዮጵያን ቤቴ ብሎ መጥራት ጀመረ።

ፌስቱላ ባደጉ አገራት ውስጥ ከጠፋ ዘመናትን አስቆጥሯል። በመሆኑም የምዕራቡ ዓለም ሐኪሞች ፌስቱላን ከትምህርት መጽሐፍ ውጭ በተግባር እምብዛም አያውቁትም።

ሐምሊኖች ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ የፌስቱላ ተጠቂዎች ሲያጋጥሟቸው አያሌ ፈተናም ነበር የገጠማቸው። የህክምና አግልግሎት ገና መዳህ እንኳ ባልጀመረበት በዛን ዘመኒቷ ኢትዮጵያ የምርምር መጽሃፍት፣ የሣይንስ ጆርናል እና ተጓዳኝ መረጃ ለማግኘት ከቶም የማይታለም በመሆኑ ሁለቱ ባልና ሚስት ከውጭው አለም ጋር መጻጻፍና መረጃ ማሰባሰብ፣ ማጥናትና ከተጨባጩ ችግር አንጻር ህክምናዊ ዘዴና ጥበብን መፍጠር ነበረባቸው።

ዶ/ር ካትሪን ስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፉ፤ "ያሰባሰብናቸውን መረጃዎች በሙሉ ካኘክናቸው በኋላ የመጀመሪያውን ፌስቱላ ለመጋፈጥ ብቃት እንዳለን ተሰማን። ለዚህም የመረጥናት ከገጠሪቷ ኢትዮጵያ የመጣችና ... ቀለል ያለ ችግር የነበራትን ወጣት ነበር። ሬጅ ኦፕሬሽኑን ሲያካሂድ እኔ ረዳቱ ነበርኩ። ከዚህ በኋላ ይህቺን መንፈስ ብርቱ፣ ርጋታ የተላበሰችና

እራሷን አሳልፋ የሰጠችንን ወጣት አስተኝተን እጅግ አስጨናቂውንና አዝጋሚ የሆነብንን የማገገሚያ ቀናት መቁጠር ጀመርን። ከ14 ቀናት በኋላ ልጅቱ እንደማንኛው ጤነኛ ሰው መሽናት ቻለች። እጅግ ደስታ ስለተሰማንም ወደ መጣችበት ቀዬ ከመመለሷ በፊት ከሬጅ ጋር ፎቶ እንድትነሳ አደረግን፤ አዲሱን ሕይወቷን ለመጀመር ከመጓዟ በፊት እጃችንን ስማ ያመሰገነችንን እስከመቼም አልረሳውም።

የጀመሩት በዚህ መልክ ነበር። ለሦስት ዓመት የፈረሙት የኮንትራት ሥራ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ በማስቆጠር ላይ በሚገኘው የሕይወት ማዳን ተልዕኮ ተቀይሮ ይገኛል። የዓላማና የመንፈስ ጽናት ያላቸው ሐምሊኖች ከምንም ተነስተው በከፈሉት ወደር የሌለው መስዋእትነት ዛሬ ከ50, 000 ሺህ በላይ ሴቶች ወገኖቻችን ከዚህ ዘግናኝ ህመም



እሷን ማዳን መቻላችን ለኛ ዘላቂ ሥራ የመሰረት ድንጋይ መሆኑን ግን አታውቅም ነበር። ከዚህ በኋላ ሁለት የፌስቱላ ተጠቂዎችን ቀዶ ህክምና አደረግናላቸው። ሁለቱም ሙሉ ለሙሉ ዳኑ" ሲሉ ገልጸዋል።

እነሆ ሐምሊኖች ለ50 ዓመታት የዘለቀውን የህይወት አድን ተልዕኮ ተፈውሰው ከህብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለዋል።

“አዲስ አበባ የሚገኘው የልዕልት ፀሐይ መታሰቢያ ሆስፒታል ነርሶችን በአዋላጅነት የሚያሰለጥን ት/ቤት ለማቋቋም የማሕጸን ዶክተሮችን ለመቅጠር ይፈልጋል”

*“ዘ ላንሰት” የእንግሊዝ የጤና መጽሔት እ.አ.አ 1957*



የሐምሊን ዜና መጽሔት በሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ክፍል በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ ለድርጅቱ ሠራተኞች የሚሰራጭ ነው፡፡

አስተያየት ወይም ለዜና የሚሆኑ ሀሳቦች ካለዎት ያድርሱን፡፡

*ሐምሊን ፊስቱላ ኢትዮጵያ*
*ኮሚዩኒኬሽን ክፍል*
*ስልክ፡+251 113 720083*
*ፋክስ፡+251 113 726252*
*ኢሜይል፡enquiries@hamlinfistula.org*
*ዌብ ሳይት፡www.hamlinfistula.org*

**Hamlin Fistula Ethiopia**

*Designed & Printed by Everest Printers*